## 3.ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት

ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በተዛባ የስርአተ ፆታ ግንዛቤ እና አስተሳሰብ ምክንያት በተለያየ መንገድ በሴቶች፣ ህፃናት እና በወንዶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት ነው። ጥቃቱ በሁሉም ፆታ እና እድሜ ክልል ላይ ባሉ ሰዎች ላይ ሊፈፀም የሚችል ቢሆንም በብዛት እና በስፋት በሴቶች ላይ ስለሚፈፀም ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በሴቶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት ተብሎ ይጠራል።

በአለም ጤና ድርጅት መረጃ መሰረት በአለም ከሶስት ሴቶች አንዷ (35%) በህይወት ዘመኗ በቅርብ በምታውቃቸው ወይም በማታውቃቸው ሰዎች አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት ይደርስባታል። በአለም አቀፍ ደረጃ በሴቶች ላይ ከሚፈፀሙ የህይወት ማጥፋት ወንጀሎች መካከል 38% የሚደርሱት በወንድ የፍቅር ጓደኛቸው ወይም የትዳር አጋራቸው የሚፈፀም ነው።

## 4.የፆታ እና ስርአተ-ፆታ ትርጉም እና ልዩነት

ፆታ ፡- ሴት ወይም ወንድ መሆን፣ ተፈጥሯዊ የሴት እና ወንድ ልዩነት ፣ የማይቀየር እና በሁሉም ቦታ እና ህብረተሰብ ተመሳሳይ የሆነ በጊዜ የማለወጥ እውነታ ነው።
ስርአተ-ፆታ፡- በማህበራዊ እና በባህላዊ የተፈጠረ (የዳበረ)የሴት እና ወንድ ልዩነት አስተሳሰብ ነው። በቦታ በጊዜ እና በየማህበረሰቡ የተለያየ ግንዛቤ እና ትርጉም ያለው እና በየዘመኑ ተለዋዋጭ ነው።

## 5.በሴቶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት አይነት

በሴቶች እና ሴት ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች በአይነታቸው እና በደረጃቸው የተለያዩ ቢሆኑም በሚከተለው መልኩ ሊዘረዘሩ ይቻላሉ።



ፆታዊ ጥቃትን መከላከል እና እንዳይከሰቱ ማድረግ የአንድ አካል ሃላፊነት ተብሎ የሚተው ጉዳይ አይደለም። ሁሉም መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ማህበራት እንዲሁም ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ከፍተኛ ሃላፊነት አለበት።

## 7.በሃገራችን ትኩረት የሚሹ የፆታ ጥቃት አይነቶች

I. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች
- ጠለፋ
- ግርዛት
- ያለእድሜ ጋብቻ
- የውርስ ጋብቻ

II. በተለያየ ሁኔታ የሚፈፀም ወሲባዊ ጥቃት
- አስገድዶ መድፈር
- ወሲባዊ ትንኮሳ

III. የቤት ውስጥ ጥቃት
- ድብደባ
- ዛቻ
- ስድብ

ከፈረንሳይ ኢንባሲ በተገኘ ድጋፍ በኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት ከዘመቻ በፆታዊ ጥቃት- ኢትዮጵያ ቡድን ጋር በጋራ በመሆን የተዘጋጀ

አድራሻ፡
የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (ኢ.ሴ.ማ.ቅ)
ስልክ፡-+251118217758/59
ፖስታ፡- 19357
ማህበራዊ ሚዲያ፡-
www.facebook.com/newa.ethiopia
www.twitter.com/cf-newa
www.newaethiopia.org



# “ሰላም ይስፈን! ፆታዊ ጥቃት ይቁም!”



# ጉዳዬ ነው!

**በማንም! የትም! ፆታዊ ጥቃት እንዲፈፀም አልፈቅድም!**

በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት በአለም ዙሪያ ከሚፈፀሙ አሳሳቢ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች አንዱ ነው። በኢትዮጵያም የተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ሴቶች የጥቃቱ ሰለባ ይሆናሉ።በፆታ ላይ የሚፈጸም ጥቃት በአመዛኙ በማህበረሰብ ውስጥ ካለው አድሎአዊ አመለካከት የሚመነጭ ሲሆን በሴቶች እና በወንዶች መካከል የሚፈጠር የስርአተ ጾታ መርህ መዛባት ውጤት ነው። ይህም በሴቶች ደህንነት፣ ጤና እና ልማት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይፈጥራል።

## 1.ጥቃት (violence)

በአለም ጤና ድርጅት ትርጓሜ መሰረት ጥቃት ማለት አካላዊ ሃይልን ወይም አቅምን በመጠቀም ሆን ብሎ በገዛ አካል ላይ፣ በሌላ ሰው፣ በቡድን ወይንም በማህበረሰብ ላይ የሚፈፀም እና አካላዊ የስነልቦናዊ ጉዳት እና ሞትን የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል የሚችል እንዲሁም እድገትን የሚያስተጓጉል የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው።

ሰዎች ሃይልን፣ ስልጣንን ወይም አቅምን ያለአግባብ በመጠቀም ጥቃት ሊፈፅሙ ይችላሉ።ይህም የሌላውን አካል ነፃ ፍቃድ በመጣስ የሚፈፀም የመብት ጥሰት ሊባል ይችላል። ጥቃቱ ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ የተጎናፀፏቸውን እና የተለያዩ አለም አቀፍ የህግ ማእቀፎች እውቅና የተሰጧቸውን ሰብአዊ መብቶች የሚጥስ ነው።

ጥቃት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመኖር ፣የነፃነት ፣የደህንነት፣ የአካላዊ እና የአእምሮ ጤንነት ፣ከማንኛውም አሰቃቂ እና ኢሰብአዊ ቅጣት እና አያያዝ የመጠበቅ፣ ሃሳብን የመግለፅ የመማር እና እራስን የማሳደግ መብቶችን የሚጥስ ወይንም ሊጥስ የሚችል ድርጊት ነው። በአጠቃላይ ጥቃት በምንም ሁኔታ እና ምክንያት ሊስተባበል እና ሰበብ ሊሰጥበት የማይችል ሙሉ ለሙሉ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ነው።

## 2.በሴቶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ትርጓሜ በሴቶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት ማለት ፆታን መሰረት አድርጎ የሚፈፀም እና በሴቶች ላይ በግል ወይም በማህበራዊ ህይወታቸው አካላዊ፣ወሲባዊ፣ስነልቦናዊ ጉዳት የሚያደርስ ወይም የሚያስከትል እንዲሁም ማስገደድ ወይም ተገቢ ያልሆነ ነፃነትን የማሳጣት ተግባርን የሚያጠቃልል ድርጊት ነው።

የሴቶች መብት የሰብአዊ መብት ነው። ስለዚህም በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውም ጥቃት የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው።

### 5.1 ኢኮኖሚያዊ ጥቃት

በተለያየ መልክ የንብረት እና የኢኮኖሚ መብት መጋፋት ወይንም መንፈግን በውስጡ ይይዛል።በተለይ ሴቶች እና ሴት ልጆች ንብረት ወይም ሃብት እንዳያፈሩ እና በንብረታቸው እንዳያዙ በማድረግ፤ የባለቤትነት መብታቸውን በመንፈግ እንዲሁም ለሰሩት ስራ ተገቢውን ክፍያ ባለመፈፀም በጥገኝነት እንዲኖሩ ማድረግን ይጨምራል። ለምሳሌ፡- የጋራ ንብረትን (ሃብት) ተጠቃሚ አለመሆን ፣ጉልበት ብዝበዛ

### 5.2 አካላዊ ጥቃት

በማንኛውም መንገድ በአካል ላይ የሚፈፀም የሃይል ጥቃት ነው።ለምሳሌ መደብደብ፣መምታት፣ መገፍተር፣ መተንኮስ እና እስከነብስ ማጥፋት ያሉትን ይጨምራል።

### 5.3 ወሲባዊ ጥቃት

ሃይልን በመጠቀም በሌላ ሰው ላይ ያለፍላጎት የሚፈፀም ማንኛውም የወሲብ ድርጊትና የወሲብ ድርጊትን የመሰሉ ለመልከም ፀባይ ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶችና ትንኮሳዎችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ አስገድዶ መድፈር፣ የወሲብ ንግድ፣ ፆታዊ ትንኮሳ፣ግብረ-ሰዶምና የመሳሰሉት ናቸው።

### 5.4 የቤት ውስጥ ጥቃት

የቤት ውስጥ ጥቃት በሃይል፣ በንግግር እና በምልክት፣ በአካል ላይ ፣ በሞራል እና ስነልቦና እንዲሁም በማንኛውም መንገድ ነፃነት በሚጋፋ ሁኔታ የሚፈፀም ጥቃትን ያካትታል። ለምሳሌ፡- ቀላል እና ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ፣ ስድብ፣ ዛቻ… ወዘተ

### 5.5 ስነልቦናዊ ጥቃት

ፆታን መሰረት በማድረግ ሆን ተብሎ የሴቶችን ሞራል እና ስሜታቸውን በሚጎዳ መል በማዋረድ እና በማሸማቀቅ የሚፈፀም ጥቃት ነው። ለምሳሌ በሰዎች፣ በስራ ባልደረቦች ፊት እና በአደባባይ ሞራል የሚነኩ ቃላትን በመጠቀም መሳደብ እና የበታች እንደሆኑ መግለፅ።

### 5.6 ማህበራዊ ጥቃት

በማህረሰቡ የተለያዩ የአመለካከትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ምክንያት በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውም የጤና፣ የስነልቦና እና የኢኮኖሚያዊ መብታቸው ላይ ተፅዕኖ ጉዳት የሚደርሱ ጥቃቶች ናቸው።
ለምሳሌ የተለያዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ጠለፋ፣ ያለእድሜ ጋብቻ እና ወ.ዘ.ተ ያጠቃልላል።

### 5.7 ፖለቲካዊ ጥቃት

ፖለቲካዊ ጥቃት በመንግስት አካላትና የፖለቲካ አመራሮች በማህበረሰብ በአጠቃላይ በተለይ ሴቶችና ሕፃናትን መጠቀሚያ በማድረግ የሚፈፀም ማናቸውንም ጥቃትን ያካትታል። ለምሳሌ የከፍተኛ የመንግስት አካላት ባላቸው ፖለቲካዊ ተፅዕኖ አማካኝነት የሚፈፀም አስገድዶ መድፍር፣ የግዴታ ጋብቻ እና ወ.ዘ.ተ

### 5.8 በግጭት ጊዜ የሚደርስ ፆታዊ ጥቃት

በተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶች እና የሰላም መናጋቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ በሚደርሰው ጥቃት ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል ከፍ ባለ ደረጃ ተጎጂ የሚሆኑት ሴቶች እና ህፃናት መሆናቸው እሙን ነው። እንደዩኒስኮ ገለፃ በግጭት ጊዜ ሴቶች እና ህፃናት ለደህንነታቸው ከለላ የሚያደርጉላቸው የቤተሰብ አባላት በተለይም ወንዶች በአካባያቸው ስለማይኖሩ ለጥቃት ተጋላጭ የመሆናቸው ሁኔታ ይበልጥ ይጨምራል። ከዚህም ባለፈ ሴቶችን ማጥቃት በግጭት ውስጥ ያለውን ማህበረሰብ እንደማጥቂ መሳሪያነት የመጠቀም ዝንባሌም በአብዛኛው ግጭት በሚከሰትባቸው በታዎች ላይ ይታያል።በግጭት ወቅት ፆታዊ ጥቃትን መፈፀም የጦር ወንጀል እንደሆነም አለምአቀፍ የጦር ህግ ይደነግጋል።

## 6. በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች የሚያስከትሉት ጉዳት

ጥቃት የተፈፃመባቸው ሴቶች ለተለያዩ ውስብስብ አካላዊ፣ ስነ-አእምሮአዊ፣ ጉዳቶች እንዲሁም ለተላላፊ በሽታዎች፣ ላልተፈለገ እርግዝና፣ የስነ-ተወልዶ እና ወሲባዊ የጤና ችግሮች እና ለሞት ይጋለጣሉ።

### 6.1 የስነልቦና እና ማህበራዊ ጉዳት
### 6.2 ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት
### 6.3 በመንግስት እና በፍትህ ስርአቱ ላይ እምነት ማጣት